DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2020-21፣ ከPre-K - 12 የውጤት ደረጃ አሰጣጥ (Grading) ፖሊሲ:

በ8.6.20 ማስተካከያ የተደረገበት (Updated)

## ዓላማ እና ስፋት (Scope)

ይህ የፖሊሲ መመሪያ፤ በትምህርት ዓመት 2020-21፣ ለኮሮናቫይረስ (COVID-19) ምላሽ በሚሰጥበት ወቅት፣ ከpre-K - 12 የውጤት ደረጃ አሰጣጥ (grading) ጋር የተያያዙ መስፈርቶችን ያስተላልፋል። በDCPS የሁለተኛ ደረጃ የውጤት ደረጃ አሰጣጥ እና ሪፖርት ማድረጊያ ፖሊሲ ውስጥ የተካተተው፣ የውጤት ደረጃ አሰጣጥ (grading) መስፈርቶች፤ በዚህ የፖሊሲ መመሪያ ውስጥ ያልተጠቀሰው፣ በስራ ላይ እንደሆነ ይቆያል።

## ሥር-መሠረት (Background) እና ንዑስ-ሃሳብ (Context)

ከዚህ በታች የተዘረዘረው፣ ለSY20-21 የውጤት ደረጃ አሰጣጥ ፖሊሲ ነው። ይህ ፖሊሲ፣ በውጤት ደረጃ አሰጣጣችን ውስጥ ባሉት፤ ፍልስፍና (philosophy) እና እሴቶች (values) ውስጥ የተተከለ ሲሆን እና በተማሪው መማር ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ በእኩልነት እና በእውነተኛነት የሚደረግ፣ በሁሉም ኢጋሮቻችን (stakeholders) የውጤት ደረጃ አሰጣጥን የተለመደ አሰራር እንዲኖረው የታሰበ ነው። በማንኛውም ይዘት ውስጥ: በመኖርያ ቤት መማር፣ በምናባዊ ወይም ሙሉ ለሙሉ በአካል መገናኘት (in-person) ውስጥም ቢሆን፤ የኮሮናቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ፣ ሁሉንም ተማሪዎች በእኩልነት እንዴት ማገዝ እንደምንችል እና የውጤት ደረጃ አሰጣጥ መመሪያውን ለመቅረጽ፣ በጥልቀት እንድናስብ አነሳስቶናል።

**ፍልስፍና (Philosophy):** በተማሪው የትምህርት ቤት ቆይታው ወቅት ያለውን የማደግ እና የእድገት ጎዳና ውጤቶችን እያስመዘገቡ እያሉ፤ ቀጣይነት ባለው መማር ላይ የውጤት ደረጃ አሰጣጥ አገልግሎቶች፣ ጊዜውን የጠበቀ አስተያየትን (feedback) መስጠት እና ግላዊ ለሆነ የትምህርት አሰጣጥን በማቀድ ላይ DCPS ያምናል።

**ዕሴቶች** (Values)፡

| **ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡** | **ደረጃዎች የሚከተሉት አይደሉም፡** |
|---|---|
| • በCCSS እና በDCPS ስርዓተ ትምህርት ላይ መሠረት በማድረግ፣ በከፍተኛ ደረጃ የተለካ የችሎታ እና የእውቀት ይዘት ባለው መልኩ የተደረገ ማስተማር እና መማር<br>• ተማሪው መሠረታዊ በሆነ የኮርስ ተሳትፎ፣ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) እና ግምገማዎችን ለማሳየት የተማሩ መሆኑን፤ በመደበኛነት ላይ መሠረት ባደረገ (standards-based) ምስክርነት<br>• ውስጣዊ ተነሳሽነትን ማሳደጊያ መሣሪያ<br>• በተወሰነው መመዘኛዎች (parameters) ውስጥ፤ ግልፅነት እና ተደጋጋሚነት በሁሉም ትምህርት ቤቶች መካከል እንዲኖር፣<br>• በአጠቃላይ በተርሙ (term) ወቅት፣ ከለሳን ለማድረግ (revision) ማግኘት የሚችል እና የሚገኝ<br>• ተደጋጋሚ (frequently) እና በትክክለኛ ሁኔታ (accurately) የተሰጠ | • በሽልማት (reward) እና በቅጣት (punishment) ባህሪይ፣ የማስተዳደሪያ መሣሪያ<br>• በተቋማት ተገዢነት ወይም ተስማሚነት ላይ መሠረት ያደረገ<br>• የዘፈቀደ እና የማጭበርበር<br>• ተርሙ (term) ከማለቁ በፊት፣ የተዘጋ ወይም ያለቀ<br>• ተማሪዎችን አንዱን አንዱ ለመለየት እና በዕድል ውስጥ ያለውን ስፋቶች ዘላቂ ለማድረግ የተጠቀሙት ዘዴ<br>• ተጠያቂነት የሚያስከትለውን ትምህርት ለተማሪዎች የማስተማሪያ መሣሪያ |

የዚህ ፖሊሲ አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታ ሆኖ የተቀመጠው፣ የውጤት ደረጃ አሰጣጥ ዘዴያችን እና የሚጠበቁባቸውን፣ **ከፍተኛ (high)** የሚጠበቁባቸውን ሁኔታን ለመፍጠር፣ ከጠንካራ እርዳታ ጋር፣ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ትርጉም የሚሰጡ አስተያየቶችን (feedback) እያገኙ፤ እንዲማሩ፣ እንዲያድጉ፣ እና ስኬታማ እንዲሆኑ መርዳት ነው። እኛ የምንጠብቀው፣ በዚህ ዓመት፣ ከመኖሪያ ቤት ውስጥም ሆነ፣ ከትምህርት ቤት፣ ወይም ሁለቱንም ያጣመረ የትምህርት አሰጣጥ ቢሆንም እኳን፤ ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ነው። በዚህ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ፣ እያንዳንዱ የDCPS ኮርስ፣ የ‘Canvas Course Companion’ ያለው እና፣ ግልጽ የሆነ በስርዓተ ትምህርት የሚጠበቅባቸው እና የሚያስፈልጉ ክንውኖችን ለተማሪዎች ያካትታል (አባሪ (Appendix) 1—ወደፊት የሚገለጽ ይሆናል)። ሁሉም የሚፈለጉ ክንውኖች፣ በተማሪው የውጤት ደረጃዎች ውስጥ የሚመደቡና የሚካተቱ ይሆናሉ። እኩልነትን፣ እንደ መፈክራችን (guidepost) በመጠቀም፣ የሚከተሉትን መመሪያዎች ለመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ አስተማሪዎች ሰጥተናል።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## የመጀመሪያ ደረጃ (Elementary) የደረጃ አሰጣጥ

ይህ ክፍል ለSY 20-21፣ የመጀመሪያ ደረጃ (elementary) ክፍሎች (PreK-5) የሚመለከት፣ የፖሊሲ መመሪያን ያቀርባል።

**Pre-K**

የቅድመ ልጅነት ትምህርት (Early Childhood Education (ECE) አስተማሪዎች፣ የልጆችን መሻሻል፤ እና በእድገታዊ ጎራዎች (developmental domains) ዙሪያ በሚገኝ እድገት፤ (በቋንቋ፣ በማንበትና መፃፍ (literacy)፣ በማስተዋል፣ በሂሳብ፣ በማህበራዊ ስሜታዊነት፣ በአካላዊ ብቃት)፤ 'Teaching Strategies GOLD system' በመጠቀም ይቀጥላል። በእያንዳንዱ የውጤት ደረጃ አሰጣጥ ወቅት፣ ልጆች ለየግል ችሎታቸው ላይ፤ ወይም በእያንዳንዱ የእድገት ማመላከቻ ውስጥ፣ ልጆቹ ከሚጠበቀው የእድገት መጠን በታች ከሆኑ፣ የሚጠበቀውን የእድገት መጠኑን የሚያሟሉ ከሆነ፣ ወይም የሚጠበቀውን የእድገት መጠን ያለፉ መሆነ፤ ማርኮችን (marks) ያገኛሉ። በ'GOLD' አማካኝነት፣ የሪፖርት ካርዶች ይዘጋጃሉ፤ ወላጆችም የልጆቹን ሪፖርት ካርዶች፣ በኦንላይን፣ በ'GOLD portal' አማካኝነት ማግኘት ይችላሉ።

**K-5**

የተርም (Term) የውጤት ደረጃ ስሌቶች፣ በተማሪው ተሳትፎ፣ ልምምድ እና ክንውኖች፣ እና ግምገማ ላይ ተመስርቶ፤ የተማሪዎን ስራ ስብጥር ባለው ባህሪው በማንፀባረቅ ይሰላል። የሁሉም ተማሪ ስራ፣ በተጨባጭነት፣ እና የውጤት ደረጃዎችን፣ በምስክርነት ላይ እና በመረጃዎች የታገዙ ሆነው ደረጃ ይሰጣቸዋል። ልክ የሆነውን ከመቶኛ የሚሰጠው ውጤት፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኛ ምርጫ ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

በምናባዊው (virtual) ዓለም፣ አስተማሪዎች በመደበኛነት ከተማሪዎች ጋር የሚጠብቋቸውን ነገሮች መንገር እና በቀለም ትምህርት ሁኔታቸው ላይ ነቅተው እንዲሰሩ በማድረግ ይከታተሏቸዋል። አስተማሪዎች፣ በሣምንት ውስጥ፣ አንድ ውጤትን ቢያንስ ቢያንስ፤ ወይም ሁለት ውጤቶችን በየ10 ቀናቶች ማጋራት አለባቸው። አስፈላጊ የሆኑ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) በሙሉ፣ እንደገና ተከልሰው ሊሰሩ የሚችሉ እና አስተማሪዎችም በደንብ እንደተረዱት ለማረጋገጥ፣ ጥራቱን የጠበቀ አስተያየት (feedback) በመስጠት ተማሪዎችን መርዳት አለባቸው።

የውጤት ደረጃዎች የሚሰጡት፣ በተርሙ ይዘት አካባቢ የስኬት ሁኔታ ላይ መሠረት በማድረግ ነው:
በመጀመሪያ (elementary) ደረጃ ላይ ያለ የስኬት መጠን፣ በተማሪው መደበኛ የሆነ እያንዳንዱ የይዘት አካባቢው በሚከተለው ሁኔታ ተመዝግበዋል:

- 4 = ከመደበኛው (standard) የበለጠ፤ (ወደፊት የገፉ/Advanced)።
- 3 = መደበኛውን (standard) የሚያሟላ፤ (ብቃት ያለው/Proficient)።
- 2 = ወደ መደበኛ (standard) እየተጠጋ የሚገኝ፤ (መሠረታዊ/Basic)፣ እና
- 1 = መደበኛውን (standard) የማያሟላ፤ (ከመሠረታዊው በታች የሆነ/Below Basic)።
- NM= ምንም ውጤት (no mark)— በዚያ ተርም (term) ወቅት፣ ላልተሰጠ ይዘት (content)

- በትምህርት ዓይነቱ ዙሪያ፣ ለችሎታዎች (skills) ወይም/የሚጠበቁባቸው (expectations)፣ የውጤቱ አካላት (sub-marks) እንደሚከተለው ተሰጥተዋል:
  - S = ጥበቃ የተደረገለት (Secure)
  - D = እድገት (Developing)፣
  - B = መጀመሪያ፣ (Beginning)[1] እና
  - N = እንዲታወቅ ያልተደረገ (Not Introduced)።

የተርሙ (Term) ውጤቶች (marks) በአስተማሪው ይወሰናል። የመጨረሻው ውጤት (Final marks)፣ የሚሰላው፣ በመጨረሻው ተርም ውስጥ በታየው መደበኛዎች (standards) ላይ መሠረት በማድረግ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ (Elementary) ሪፖርት ካርዶች፣ ጥርቅም ውጤቶችን (cumulative marks) አይጨምሩም።

1 Note: Currently DCPS uses "B = Basic." The proposed new report card would switch the language to "B = Beginning" per 5-B DCMR §2200.6.

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## የሁለተኛ ደረጃ (Secondary) የውጤት ደረጃ አሰጣጥ

ይህ ክፍል የሁለተኛ ደረጃ (secondary) ክፍሎች፣ (6 - 12)ን የሚመለከት ነው።

**<u>የተርም (Term) ደረጃዎች</u>**

**የተርም (Term) ደረጃ የሚሰላው፣ በተማሪው ተሳትፎ (Student Engagement)፣ (20%)፤ ልምምድ እና ክንውን(Practice & Application)፣ (40%) እና ግምገማ (Assessment)፣ (40%) ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣** የተማሪውን ስራ ስብጥር ያለው ባህሪውን በማመላከት ይሆናል። የሁሉም ተማሪ ስራ በተጨባጭነት (objectively) እና በተከታታይ (consistently) ውጤት የሚሰጣቸው እና ውጤቶች በማመሳከሪያዎች ጋር እና በመረጃዎች ይደገፋሉ።

ምድቦች እና ምዘናዎች፣ በቅድሚያ የሚከተቱት (pre-populated)፣ በአስተማሪዎች የውጤት መጽሀፍት (gradebooks) ውስጥ የሚገቡት እና የሚተረጎሙት ከታች እንደተመለከተው ነው:

**የተማሪ ተሳትፎ (Student Engagement) (20%)**: *(ከዚህ በፊት የተማሪ መካፈል (student participation) ተብሎ ይጠራ የነበረው)*: ይህ ምድብ፣ ጊዜያቸውን እና ስራቸውን ለመቆጣጠር እና ስራቸውን በዕቅዶቻቸው መሠረት እንዲያጠናቅቁ፤ ሳምንታዊ የስራ ዕቅዶችን መፍጠርን ጨምሮ፤ በበርካታ መንገዶች አማካኝነት በትምህርት ቤት ንቁ ተሳትፎን ማካተትን ጨምሮ ያሳያል። የስራ ዕቅዶች፣ የየግል ክለሳዎችን ወይም የስራ ማራዘሚያዎችን እንደየአስፈላጊነቱ ሊጨምር ይችላል። በተጨማሪም፣ ለመስማት፣ ለመናገር፣ ለመፃፍ፣ እርስ በርስ ለመወያየት፣ እና/ወይም በክፍል ውይይቶች ወይም በቡድን እንቅስቃሴዎች ወቅት የአመራር ቦታን መውሰድን ጨምሮ ለክሬዲት ምስክር ሊሆኑ የሚችሉን፣ በዚህ ምድብ ሊካተቱ ይችላሉ። ተሳትፎ፣ ለተማሪ መማር እገዛ ያደርጋል። መቅረት፣ ከተሳትፎ የውጤት ደረጃ ጋር አብሮ የሚፈረጅ አይሆንም።

**ልምምድ እና ክንውን (Practice & Application) (40%)**: ይህ ምድብ፣ በአጠቃላይ በክፍሉ በተሰጥው የየግል ትምህርት ውስጥ የተገኘውን ጥንቅቅ ያለ እና ጥርቅም ያለው ችሎታዎችን፤ ለመለማመድ እና ለመጠቀም፤ የሁሉንም ተማሪዎች የስራ ውጤቶች ይጨምራል።
የቤት/የክፍል ስራዎች (Assignments)፣ ተማሪዎች ችሎታቸውን በተሳካ ሁኔታ ማዋሃድ እንዲችሉ እና በክንውኖች እና ልምምድ አማካኝነት ይዘቶችን ለማግኘት ያስችላቸዋል። በ'Canvas Course Companions' ውስጥ አስፈላጊ የሆኑት የስርዓተ ትምህርት ክንውኖች፤ በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኝ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments)ን ይጨምራል። በእነዚህ ክንውኖች የችሎታ ብቃታቸውን ማሳየት ያልቻሉ ተማሪዎች፣ የተወሰነ ብቃት ያለው ክንውኖችን እንደገና እንዲከልሱ የሚያደርጋቸው፤ የውጤት ደረጃን ለማሳደግ እና የችሎታ ብቃታቸውን አሳድጎ ለማሣየት የሚያስችላቸውን አስተያየቶች (feedback) ያገኛሉ። በዚህ ዙሪያ የሚሰራ ስራ፣ በክፍሉ ክንውን ወቅት፣ ውስብስባዊ የአሰራር መንገድን ለማሳደግ፣ ስብስብን የሚያካትት ግምገማዎችን መገንባት አለበት። እነዚህ ግምገማዎች በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጪ ሊጠናቀቁ ይችላሉ። እነዚህ ግምገማዎች፣ በአስተማሪዎች፣ በእኩዮቻቸው ወይም በመገኛ ምንጮች (resources) መታገዝ ይችላሉ።

**ግምገማ (Assessment) (40%)**: ይህ ምድብ፣ በየግል የተማሪ ችሎታዎችን፣ እውቀትን፣ እድገትን እና ጉብዝናቸውን ጨምሮ ሁሉንም መደበኛ ግምገማን ያካትታል። በ'Canvas Course Companions' ውስጥ የሚፈለጉ የስርዓተ ትምህርት ክንውኖች የግምገማ ሁኔታዎች፣ ከተለመደው የፈተናዎች (tests) እና ጥያቄዎች (quizzes) ጀምሮ እስከ በአጠቃላይ ክፍሉ ውስጥ የተማሪውን ችሎታ እና እውቀት ሊያሳይ በሚችል በአሰራር ላይ መሠረት ያደረገ (performance-based) ክንውኖች መካከል ባለው ስፋት ይከናወናል። ግምገማዎች በየግል (independently)፣ በተሰጠ የተወሰነ ሰዓት፣ እንክብካቤዎችን በማክበር፣ በመደበኛ ፈተና መስጫ ቦታዎች (በምናባዊነት (virtually) ሊስተካከሉ የሚችሉ መልኩ) መጠናቀቅ አለባቸው። በዲስትሪክቱ ወይም በአስተማሪዎች ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል። ብቃታቸውን ለማሳየት ያልቻሉ ተማሪዎች፤ የተወሰነ ጥራት ያለው አስተያየት (feedback) በድጋሚ በከለሱት ወይም ተደግሞ በተሰጣቸው ግምገማ መሠረት፣ የውጤት ደረጃን እና ብቃታቸውን ማሳደግ እንደቻሉ ማሳየት አለባቸው።

መስፈርቶች እና ተመራጭ የሆኑ ልምዶች (Best Practices)

- አስተማሪዎች፣ *ቢያንስ 2 የውጤት ደረጃዎችን በየ10 ቀናቶች ውስጥ* ይጭናሉ (post ያደርጋሉ)። ይህ የመነሻ ቦታ (floor) እንጂ ጣሪያ (ceiling) አይደለም። ተማሪዎች ነጥቦችን ለማግኘት፣ በርካታ ዕድሎችን ማግኘት አለባቸው።
- አስተማሪዎች፤ ቢያንስ 9 የቤት/የክፍል ስራዎችን (assignments) ለተርሙ (Term) ውስጥ ካላስገቡ፤ የተርም የውጤት ደረጃን (Term grade) ከማስገባት ይከለከላቸዋል።
- የውጤት ደረጃ አሰጣጥ መጽሐፍት (Gradebooks)፣ የቤት/የክፍል ስራ (assignment) የውጤት ደረጃዎች ጊዜያቸውን ጠብቀው ለመጫናቸው ሣምንታዊ ቁጥጥር ያደርጋል።
- ከ'Canvas Course Companions' ላይ፣ ሁሉም የሚፈለጉ የስርዓተ ትምህርት ክንውኖች (Curricular Tasks)፤ ለክለሰ ስራ የተመቻቹ እና ተማሪዎች የቤት/የክፍል ስራዎችን (assignments) ላይ ክለሳን በሚያደርጉ ጊዜ በደንብ እንዲገባቸው ለመርዳት፤ አስተማሪዎች አስተያየቶችን (feedback) መስጠት አለባቸው። አስተማሪዎች ክለሳ የተደረገባቸውን የቤት/የክፍል ስራዎችን (assignments) ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ የውጤት ደረጃ ሰጥተውና አስገብተው መገኘት፣ መስፈርቱ በሚጠይቀው መሠረት ቢያንስ በየ10 ቀናቶች ውስጥ አዲስ ወይም ማስተካከያ (updated) ማስገባት አለባቸው።

- ተማሪዎች ስራዎቻቸውን ዘግይተው ስላስገቡ አይቀጡም።
- ለቤት/ክፍል ስራዎች (assignments)፣ የነጥብ ዋጋዎች፡ 10፣ 20፣ 25፣ 50 ወይም 100 ናቸው። ሁሉም ምድቦች በርካታ የሆኑ የቤት/የክፍል ስራዎች (assignments) ሊኖራቸው ይገባል።
- የክለሳ ስራዎች (Revision work)፣ የተለየ የውጤት ደረጃ ወይም ወደ ዋናው የውጤት ደረጃ ሊደመር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፤ በሁለቱም መንገድ ቢሆን፤ በዋናው የውጤት ደረጃ ላይ የክለሳ ስራው (revision work) ያሳየውን ተጽዕኖ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች እንዲያዩት የሚፈቅድ መንገድ መካተት አለበት።

**<u>የመጨረሻ የውጤት ደረጃዎች</u>**

የመጨረሻ የኮርሱን የውጤት ደረጃን ለማስላት፣ እያንዳንዱ የተርም የውጤት ደረጃ፣ በ0 እና በ4 መካከል የዋጋ አማካኝ (averaged) ተሰጥቶት፣ (ከዚህ በታች እንደተመለከተው) ይመደባል። የተገኘው የመጨረሻ የውጤት ደረጃ (final grade) በአማካኝነት በተሰጠው የተርም የውጤት ደረጃዎች ላይ ባለው የነጥብ ዋጋው ላይ መሠረት አድርጎ የሚገኝ ይሆናል።
**በSY20-21 የተደረገ ብቸኛ ማስተካከያ፣ የመካከለኛ ተርሞች (midterms) እና የመጨረሻ ፈተናዎች (final exams)፣ አሁን የሚሠሉትን ከተርሙ (term) የውጤት ደረጃዎች ውስጥ እንጂ ለየብቻቸው እንደማይሰሉ፣ እባክዎን ያስተውሉ።** ይህ ቻርት (chart)፣ በመጨረሻ የውጤት ደረጃ ስሌት ላይ፣ ግልጽነትን (transparency) እና ግንዛቤን ለማሳደግ የተዘጋጀ ነው።

| በተርም (Term) ከመቶኛ የተገኘ | በተርም (Term) ውጤት (Grade) የተመደበ | ለደረጃው የተመደበ ዋጋ (Value) | የመጨረሻ ውጤት ስሌት ማብራሪያ (Final Grade Calculation Explanation) | ገደብን በወከለ ሁኔታ የተሰላ የነጥብ ዋጋ (Calculated Point Value Range Represented) | መጨረሻ የተገኘ የውጤት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 92.5% እስከ 100% | A | **4.0** | **አንድ ነጠላ ተርም (Single Term):** በአንድ ነጠላ ተርም (single term) ውስጥ፣ ተርሙ (term) ውጤት የሚሰጣቸው ኮርሶች፣ የመጨረሻ ውጤት (final mark) ነው።<br><br>**ሁለት ተርም (Two Term):** በሁለት ተርም ሴሚስተር (semester) ውስጥ፣ በምድብ ክፍሉ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ በሁለት ተርም (two term) የውጤት ዋጋዎች ያላቸው ኮርሶች፤ የመጨረሻ ውጤቱን (final mark) ዋጋውን ለማግኘት እና ውጤቱን ለመስጠት፣ በሁለት በመደመር እና በማካፈል ይሰላሉ።<br><br>**አራት ተርም (Four Term):** በአራት ተርም (four term) በዓመቱ ሙሉ (yearlong) ውስጥ፣ በምድብ ክፍሉ ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ በአራት ተርም (four term) የውጤት ዋጋዎች ያላቸው ኮርሶች፤ የመጨረሻ ውጤቱን (final mark) ዋጋውን ለማግኘት እና ውጤቱን ለመስጠት፣ በአራት በመደመር እና በማካፈል ይሰላሉ።<br><br>***ማንኛውም የሚሰጡ ፈተናዎች (exams)፣ በተርሙ (term) በተወሰደበት ወቅት ውስጥ፣ በግምገማ ምድብ ውስጥ የሚካተት፣ እና ለብቻ ለነጥሎ የሚሰላ አይሆንም።*** | ከ3.7 የበለጠ እና ከ4.0 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **A** |
| 89.5% እስከ 92% | A- | **3.7** | | ከ3.3 የበለጠ እና ከ3.7 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **A-** |
| 86.5% እስከ 89% | B+ | **3.3** | | ከ3.0 የበለጠ እና ከ3.3 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **B+** |
| 82.5% እስከ 86% | B | **3.0** | | ከ2.7 የበለጠ እና ከ3.0 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **B** |
| 79.5% እስከ 82% | B- | **2.7** | | ከ2.3 የበለጠ እና ከ2.7 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **B-** |
| 76.5% እስከ 79% | C+ | **2.3** | | ከ2.0 የበለጠ እና ከ2.3 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **C+** |
| 72.5% እስከ 76% | C | **2.0** | | ከ1.7 የበለጠ እና ከ2.0 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **C** |
| 69.5% እስከ 72% | C- | **1.7** | | ከ1.3 የበለጠ እና ከ1.7 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **C-** |
| 66.5% እስከ 69% | D+ | **1.3** | | ከ1.0 የበለጠ እና ከ1.3 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **D+** |
| 63.5% እስከ 66% | D | **1.0** | | ከ0.7 የበለጠ እና ከ1.0 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **D** |
| 63 እና በታች | F | **0** | | ከ0.7 ያነሰ ወይም እኩል የሆነ | **F** |

አንድ ጊዜ የመጨረሻ ውጤቶች (final grades) በአስፐን (Aspen) ውስጥ ከተሰላ በኋላ፣ ከዚህ በላይ ያሉት ዋጋዎች (values) በአስፐን (Aspen) የሚቀመጡ እና በሚከተለው መሠረት፣ በተማሪው የትምህርት ውጤት ማስረጃዎች (transcripts) እና ሪፖርት ካርዶች ላይ የሚታተሙ ይሆናል:

| ከA-F በሆነ መለኪያ ላይ የተገኘ የውጤት ደረጃ | በትምህርት ውጤት ማስረጃ (Transcript) ላይ የታተመ የውጤት ደረጃ | ምክንያት (Rationale) |
|---|---|---|
| A | A | A ወይም B ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህን ውጤት፣ በትምህርት ውጤት ማስረጃቸው (transcript) ላይ እንዲታተም እና ለGPA ክብደት ከሚሰጥ ተያያዥነት ላይ እንዲታይ ጥቅም ያስገኝቸዋል። |
| B | B | |
| C | P | C ወይም D ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህ አነስተኛ የሆነ የውጤት ደረጃ በመታተሙ ቅጣት ላይ አይጥላቸው። ይልቁንም፣ የ"P" (አልፏል የሚለውን ለማሳየት) ይሰጣቸው እና በGPA ላይ ደግሞ ገለልተኛ (neutral) ሆኖ ይታያል። |
| D | P | |
| F | I | የመውደቅ የመጨረሻ የውጤት ደረጃ ያገኙ ተማሪዎች፣ የ"I" ያላጠናቀቀ (incomplete) ተብሎ እንዲሰየም ይደረጋል። |

- የ"I" ያላጠናቀቀ (incomplete) ተብሎ በመጀመሪያ ሴሚስተር የተመደቡ ተማሪዎች፣ በኮርሱ ለማለፍ፣ ኮርሱን በሁለተኛው ሴሚስተር ሊደግሙት ይችላሉ።
- "I" የተሰጣቸው ተማሪዎች፣ እስከ 2021 የበጋ (summer) ትምህርት ቤት መጨረሻ ድረስ፣ በኮርሱ የማለፊያ ውጤትን ለማግኘት ጊዜ ይኖራቸዋል። ይህን እስከዚያን ቀን ድረስ ካላደረጉ፣ የ"I" ውጤቱ ወደ "F" ይቀየር እና ተማሪው ኮርሱን እንዲደግም ይደረጋል።
- C እና D ፊደል በውጤት ደረጃቸው ("P" ሆኖ ከመፃፍ ይልቅ) እንዲሆንላቸው የሚፈልጉ ተማሪዎች፤ ወይም የA እና B ፊደል በውጤት ደረጃቸው ላይ እንደ "P" ሆኖ እንዲታተም (A ወይም B ሆኖ ከመፃፍ ይልቅ) የፈልጉ ተማሪዎች፤ ይህንኑ በትምህርት ውጤት ማረጋገጫቸው (transcript) ላይ እንዲስተካከል፣ የትምህርት ቤት ካውንስለራቸውን ማነጋገር አለባቸው።

## የ'Opportunity Academies' እና የክሬዲት ማካሻ (Credit Recovery)

### የ'Opportunity Academy' የውጤት ደረጃ አሰጣጥ

የ'Opportunity Academies'፣ በአንድ ነጠላ የሆነ የተርም (single term) የውጤት ደረጃ አሰራር ላይ መስራቱን ይቀጥላል። አንድ ጊዜ ተማሪው ኮርሱን ካጠናቀቀ በኋላ፣ የመጨረሻ ውጤቱ በአስፐን (Aspen) ውስጥ ይከተት እና በውጤት ማረጋገጫው (transcript) ላይ ከላይ እንደተመለከተው ይታያል። "I" የተሰጣቸው ተማሪዎች፣ በኮርሱ የማለፊያ ውጤትን ለማስመዝገብ እስከ 2021 በጋ (summer) ትምህርት ቤት ድረስ፤ ጊዜ ይኖራቸዋል። ይህን እስከዚያን ቀን ድረስ ካላደረጉ፣ የ"I" ውጤቱ ወደ "F" ይቀየር እና ተማሪው ኮርሱን እንዲደግም ይደረጋል።

### ክሬዲትን መልሶ ማካሻ (Credit Recovery) የውጤት ደረጃ አሰጣጥ

የክሬዲት ማካሻ (Credit recovery) ኮርሶች በአጠቃላይ በSY20-21 በሙሉ መሠጠት አለበት። እነዚህ ክፍሎች በተወዳዳሪነት ላይ መሠረት ያደረገ (competency-based) እና በየግል የአሰራር የፍጥነት አካሄድ (self-paced) ላይ ተመርኩዞ የተቀረጸ በመሆኑ ምክንያት፣ ከውጤት ደረጃ አሰጣጡ የሚጠበቀውም፣ እንደዚሁም በአንድ ዓይነት ሁኔታ በተለየ የማስተካከያ መለኪያዎች እና ስሌቶች ላይ ከላይ ተገልጸዋል። እንደ ሁልጊዜውም፣ የውጤት ደረጃ በሚከተሉት ላይ መሠረት ማድረግ አለባቸው:

- 50% የተማሪ ልምምድ እና ክንውኖች (Student practice & application)
- 50% ግምገማ (Assessment)

የመጨረሻ የክሬዲት ማካሻ (credit recovery) የውጤት ደረጃዎች እንደሚከተለው ይፃፋሉ:

| ከA-F በሆነ መመዘኛ፣ የተገኘ የውጤት ደረጃ | በትምህርት ውጤት ማስረጃ (Transcript) ላይ የታተመ የውጤት ደረጃ | ምክንያት (Rationale) |
|---|---|---|
| A | A | A ወይም B ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህን ውጤት፣ በትምህርት ውጤት ማስረጃቸው (transcript) ላይ እንዲታተም እና ለGPA ክብደት ከሚሰጥ ተያያዥነት ላይ እንዲታይ በማድረግ ጥቅም ያስገኝቸዋል። |
| B | B | |

| | | |
|---|---|---|
| C | P | C ወይም D ያገኙ ተማሪዎች፣ ይህ አነስተኛ የሆነ የውጤት ደረጃ በመታተሙ ቅጣት ላይ አይጥላቸው። ይልቁንም፣ የ“P” (አልፏል የሚለውን ለማሳየት) ይሰጣቸው እና በGPA ላይ ደግሞ ገለልተኛ (neutral) ሆኖ ይታያል። |
| D | P | |
| የክሬዲት ማካካሻ (credit recovery) ኮርስን ማጠናቀቅ ያልቻሉ ተማሪዎች፣ የ“W” (የለቀቀ/withdrawn) የሚለው ውስጥ ይመደባሉ። | | |

- ተማሪው ከዚህ ቀደም ‘F’ ያገኘበትን ክፍል፣ የክሬዲት ማካካሻ (credit recovery) ኮርስን የሚወስድ ከሆነ፣ አዲሱ የውጤት ደረጃው፤ ከዚህ ቀደም በተማሪው የትምህርት ውጤት ማስረጃው (transcript) ተመዝግቦ የነበረውን የ‘F’ ውጤትን አይተካውም።
- የ“I” (ያልተጠናቀቀ/incomplete) መፍትሄ ለመስጠት፣ ተማሪው የክሬዲት ማካካሻ (credit recovery) ኮርስን የሚወስድ ከሆነ፣ ተማሪው የ“P” ውጤትን ሊያገኝ የሚችል ሆኖ፤ የ“I” ውጤቱንም ይተካዋል።

## የተማሪን እድገት ሪፖርት ማድረግ እና መርዳት

ማስታወቂያ

ወላጆች እና ተማሪዎች፣ በጽሁፍ እና በመደበኛ ሁኔታ (ቢያንስ በእድገት ሪፖርት ማድረጊያ እና በሪፖርት ካርድ ጊዜያት)፣ የተማሪዎችን ወደ መደበኛ ይዘቱ ስኬት ያደረጉትን የእድገት ሂደትን ያሳውቃል። ለዚያ ስኬት እንዲያበቃቸው፣ ስለልጃቸው የቀለም ትምህርት፣ የማህበራዊ፣ ወይም የባህሪ እድገት ላይ ስላላቸው ስጋቶች ሊያነጋሩ የሚችሉትን የሠራተኛ አባል ስም እና የአድራሻ መረጃዎቻቸውን፣ በSeptember ወር መጨረሻ ላይ፣ ወላጆች ማግኘታቸው ለማረጋገጥ ርዕሰ መምህሮች (principals) ኃላፊነት ይወስዳሉ።

የእድገት ሪፖርቶች

የእድገት ደረጃ መግለጫ ሪፖርቶች (Progress reports)፣ ለሁሉም ተማሪዎች በእያንዳንዱ ተርም (term) መካከል (midpoint) የሚሰጡ ይሆናል። ወደ መደበኛ ይዘት ስኬት የሚደርገው ጉዞ ላይ፣ ለውጦች ካሉ ወይም ተማሪዎች አጥጋቢ የሆነ እድገት ማሳየታቸውን እንዲቀጥሉ ለማበረታታት፤ አስተማሪዎች እድገቱን በተመለከተ፣ የደረጃ ውጤቶችን እና አስተያየቶችን በማመላከት ይሰጣሉ። የአስተማሪው አስተያየቶች፣ C ወይም ከዚያ በታች ላመጡ ተማሪዎች ያስፈልጋቸዋል። አስተያየቶቹ፣ ተማሪው ለምን በትግል ላይ እንዳለ ወይም ለምን እየወደቀ እንደሚገኝ እና እርሱ/እርሷ በክፍል እድገቱ/ቷ ለማለፍ ወይም ለማሻሻል ምን እንደሚያስፈልጋቸው በትክክል ይገልፃል።

ከእድገት ሪፖርቶቹ (progress reports) በተጨማሪ፣ ልጃቸው በማንኛውም የተርሙ ጊዜ ውስጥ፣ በመውደቅ አደጋ ላይ የሚገኝ ከሆነ እና ተገቢ መስሎ ከታያቸው፣ ተማሪውን ወደ ተማሪ እርዳታ ቡድን (Student Support Team (SST) መምራታቸውን፣ አስተማሪዎች ለወላጆች በጽሁፍ ያሳውቃሉ። ሁሉም ተማሪዎች፣ ምንም እንኳን የእድገት ሪፖርታቸውን (progress report) ሲቀበሉ፣ እየወደቁ መሆኑን ቢያሳይም እኳን፣ ስኬታቸውን ለማስመስከር የሚችሉበትን እድል ሊሰጣቸው ይገባል። አስተማሪዎች፣ ከተመደበላቸው ሠራተኛ፣ ከተማሪው ወላጅ(ጆች)፣ እና ከተማሪው ጋር ሆነው በመስራት፣ ተገቢ የሆነ ጣልቃገብነትን ለይቶ ለማወቅ አብረው መስራት አለባቸው።

ሪፖርት ካርዶች

ሪፖርት ካርዶች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ ተርም መጨረሻ ላይ ይሠጣል፤ ይህም የተማሪውን፣ የእያንዳንዱን የመጨረሻ ተርም የውጤት ደረጃ አካትቶ የያዘ ይሆናል። ሪፖርት ካርዶች (Report cards)፣ ተርሙ (term) ካለቀ በአስራ ሁለት (12) የትምህርት ቀናት ውስጥ መሰጠጥ ይኖርበታል።

የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች (Parent-Teacher Conferences)

የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎች፣ በተማሪው ወላጅ እና ተማሪው በሚማርበት ክፍል፣ ኮርስ፣ ወይም የትምህርት ዓይነት ላይ አስተማሪ በሆነው መካከል፣ የጊዜ ሰሌዳ የተያዘላቸው የስብሰባ ዓይነቶች ናቸው። ተማሪዎች በዚህ ዓይነቱ ስብሰባዎች ላይ እንዲካፈሉ ማድረግ ተመራጭ የሆነ ተሞክሮ ነው። እነዚህ ዓይነት ስብሰባዎች፣ ስለተማሪው እድገት ለወላጅ እና ለተማሪ ለመግለጽ የተዘጋጀ እና ወላጅ እና አስተማሪ፣ ተማሪው ስኬትን እንዲያገኝ፤ ስለስልቶች፣ እርዳታዎች፣ እና ዕቅዶች ላይ ይወያያሉ። በስብሰባው ላይ ውይይት ሊደርግባቸው ከሚችሉ ርዕሶች መካከል፤ የቀለም ትምህርቶች፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) እና ባህሪ (behavior) አካቶ ሊይዝ ይችላል። የወላጅ-አስተማሪ ስብሰባዎቹ (Parent-teacher conferences)፣ በተርሙ (term)፣ F (I) ያገኙ ተማሪዎች፣ የሪፖርት ካርድ ከተሰጠበት ቀን በሁለት ሣምንታት ውስጥ መካሄድ አለበት። ተማሪው በበርካታ ክፍሎች ውስጥ የF (I) ውጤት አግኝቶ ከነበረ፣ አስተማሪዎች የጣምራ ስብሰባን ከወላጆች ጋር ሊያደርጉ ይችላሉ።

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

## የመውደቅ የውጤት ደረጃዎችን እያገኙ ላሉ ተማሪዎች እርዳታ መስጠት

የመውደቅ የውጤት ደረጃዎች ያላቸውን፣ ወይም የመውደቅ አደጋ ላይ ለሚገኙ ሁሉንም ተማሪዎች፣ የትምህርት አሰጣጥ እርዳታ ዕቅዶች ሊቀረጹላቸው ይገባል።

እነዚህ ዕቅዶች ሊኖራቸው የሚገባው፤

እያንዳንዱን ተማሪ በደረጃው/ዋ መሻሻልን ለማሳየት ባላቸው ፍላጎቶች ላይ እና እንዴት እንደሚገመገሙ መለየት የIEP ወይም የ504 ዕቅድ ላላቸው ተማሪዎችም ጭምር የእርዳታ ዕቅድ ሊኖራቸው ይችላል። የትምህርት አሰጣጥ እርዳታ ዕቅዶች፤ በሚወስዱት በጊዜ ርዝመት እና ጥልቀት እና በአሁኑ ጊዜ ከሚሰጠው የትምህርት ቤት ልምዶች፣ የዕቅድ ጣልቃገብነት፣ እና የSST ሂደት ጎን ለጎን ሆነው መካሄድ አለባቸው። ሁሉም ዕቅዶች በአስተማሪዎች ተመዝግበው የሚያዙ እና የሚፈቀዱ ቢሆኑም፤ ተማሪዎች የራሳቸው የሆነ የዕቅድ ረቂቅን የማዘጋጀት ዕድል ሊሠጣቸው ይገባል። አስተማሪዎችም፣ የተወሰዱትን ጥረቶች በሙሉ በጽሁፍ መዝገብ በመያዝ፣ ከተማሪ እና ወላጅ ጋር ለመነጋገር ማቀድ ያስፈልጋቸዋል። የዕቅዶቹ ቅጂዎች፣ ለተማሪው ወላጅ(ጆች) መቅረብ እና በተማሪው ፋይል ውስጥ መቀመጥ አለበት። እያንዳንዱ አዋቂ ተማሪ፣ ወይም ለአቅመ አዳም ያልደረሰ (minor) ተማሪ ወላጅ፣ የተማሪው አልፎ በተዘዋወረበት ሶስተኛ ተርም (term ) ከተዘጋ በኋላ፣ ወይም የምርቃት ሁኔታው ከታወቀ በኋላ፤ በ12 የትምህርት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት። በኮርሱ ወይም በክፍሉ መደበኛዎቹን (standards) ያላሟላ ማንኛውም ተማሪ፣ በበጋ (summer) ትምህርት ቤት ለመመዝገቢያ በቂ ጊዜ መኖሩን ለማረጋገጥ፤ ከመጨረሻ የትምህርት ቀንን ሳያልፍ፣ ባለው ጊዜ ውስጥ እንዲያቁት መደረግ አለበት። ከክፍል ወደክፍል ስለማለፍ እና ምርቃት የሚመለከት መመሪያም በቅርቡ በቀጣይነት ይቀርባል።

## በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (Attendance) እና የደረጃ አሰጣጥ

ዝቅተኛ የሆነ፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance)፣ ተማሪዎች፤ በእርግጠኝነት በበቂ ሁኔታ እድገት እንዳያሳዩ እና ኮርሳቸውን እንዲወድቁ የሚያደርጋቸው ምክንያት በመሆኑ፤ አስተማሪዎች፣ የተማሪውን መደበኛ የሆነ ተሳትፎን መቆጣጠር ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም፣ የኮርስ ደረጃ ላይ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ላይ የሚወሰድ ባለመሆኑ ምክንያት፣ በኮርስ (course) መውደቅ፣ ከSY20-21 በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) ጋር አይገናኝም።